## ምዕራፍ ፲፪

### ዘሆሣዕና ምንባብ

፩ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ ፩ አምላከ ናዝራውያን፡ዓምደ ሃይማኖትነ ዘኢይጸንን፡ሠርዌ ሐመርነ ዘኢይተነትን፡ብርሃነ ማኅቶትነ ዘኢይዴምን፡ኅቡረ ህላዌ ዘእምቅድመ አዝማን፡ብሑተ ስም ወሥልጣን፡ጽምረተ መለኮቱ ዘእንበለ ፍልጣን፡ርኅበ መንግሥቱ ዘኢይትዌሰን፡ወክበደ ብዕሉ ዘኢይትመጠን፡ሎቱ ይደሉ ስብሐት እምአፈ መላእክት ትጉሃን፡ወእምአፈ ኲሎሙ መሀይምናን፡እለ ተሐፅኑ በሐሊበ አጥባቲሃ ለቤተክርስቲያን፡፡ ለዓለመ ዓለም አሜን፡ ወአሜን፡፡

፪ ድርሳን ዘደረሰ ፩ እምርቱዓን ሃይማኖት በዘይጸንዕ ሕንጻ ሥጋሆሙ ለመሀይምናን በኢየሱስ ክርስቶስ ቃለ ተጋንዮ ዘይትነበብ በእሑደ ሆሳዕና፡፡ይቤ ልሳን ይደክመኒ ለነቢብ ወመንፈስ ያጔብረኒ ለተናግሮ፡፡ልቡናየ ስእነ በጺሐ ኀበ ዘኀለይኩ፡፡ወሠረገላ መንፈስ ቅዱስ መስጠ ወአብጽሖ ኀበ ዘፈቀደ፡፡ ክርሥየ ንህከት ለትካዘዘ ዓለም ወፍቅረ ኢየሱስ ክርስቶስ ዔወዋ ለልብየ መንግሌሁ፡፡አፉየ ለስሐ እምጣዕመ ቃል ወሊቀ ካህናት ዐቢይ ቀሰሞ በዔወ መለኮቱ፡፡እገርየ ተንተና ለወዲቅ ወእግዚአብሔር ሶቀኒ በየማኑ፡፡ሞገደ አዝማን ሆኮ ለሐመረ ልብየ ወሊቀ ኖትያት ሐደፈኒ በመቃድፈ ጥበቢሁ፡ተንሥኡ ላዕሌየ መራደ ጸላዒ ወመኰንነ ጽድቅ ፀብኦሙ በሰይፈ ቃሉ፡ለውለወ ልሳና ከይሲ ምሉዐ ሕምዝ ወእግዚአብሔር ለጐሞ በልጓመ ቅኔሁ፡፡ ምንተኑ አዐስዮ ለእግዚአብሔር በእንተ ኲሉ ዘገብረ ሊተ፡፡ወእምይእዜሰ ይደልወኒ ከመ እበል ዘልፈ እሬእዮ ለእግዚአብሔር በቅድሜየ በኲሉ ጊዜ፡፡እስመ እምየማንየ ውእቱ ከመ ኢይትሀወክ፡፡በእንተዝ ተፈሥሐ ልብየ ወተሐሥየ ልሳንየ፡፡ መዝ ፲፰÷፰-፱

፫ ወዓዲ ይደልወኒ ከመ እበል ለምንት ትቴክዚ ነፍስየ ወለምንት ተሀውከኒ፡፡እመኒ በእግዚአብሔር ከመ እገኒ ሎቱ መድኃኔ ገጽየ አምላኪየ፡፡ወካዕበ ይደልወኒ ከመ እበል እግዚአብሔር ያበርሀ ሊተ ወያድኅነኒ ምንትኑ ያፈ

## ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት

### የሆሣዕና ምንባብ

፩ በአብና በወልድ በመንፈስቅዱስ ስም አንድ የናዝራውያን አምላክ የማይለወጥ የሃይማኖት ምሰሶ የማይፍገመገም የመርከባችን አለቃ የማይጨልም የፋናችን ብርሃን ከዘመናት አስቀድሞ በህልውና አንድ የሆነ በስምና በሥልጣን የሠለጠነ የመለኮቱ አንድነት የማይለወጥ የመንግሥቱ ስፋት የማይወሰን የብልጥግናው ክብደት የማይለካ ከትጉሃን መላእክት አንደበት በቤተክርስቲያን በጡቶቿ ወተት ካደጉ ከምእመናንም ሁሉ አንደበት ለርሱ ምስጋና ይገባል ለዘላለሙ አሜን አሜን፡፡

፪ የምእመናን የአካላቸው ሕንፃ በኢየሱስ ክርስቶስ በሚጸና ገንዘብ ሃይማኖታቸው ከቀና ሰዎች አንዱ የደረሰው ድርሳን፣ በሆሣዕና እሑድ የሚነበብ የመማፀን ቃል፡፡ አንደበት ለመናገር ይደክመኛል አለ መንፈስ ግን ለመናገር ግድ አለኝ፡፡ ልቤ ካሰብሁበት ለመድረስ ተሳነው የመንፈስቅዱስ ሠረገላ ግን ነጥቆ ወደ ወደደው አደረሰው÷ ሆዴ ለዚህ ዓለም አሳብ ተከዘች የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ግን ልቤን ወደርሱ ማረካት ከቃሉ ጣዕም የተነሣ አንደበቴ አልጫ ሆነ ታላቁ የካህናት አለቃ ግን በመለኮቱ ጨውነት አጣፈጠው÷ እግሮቼ ለመውደቅ ተፍገመገሙ እግዚአብሐር ግን በቀኙ ደገፈኝ፡፡ የዘመናት ሞገድ የልቤን መርከብ አናወጸው የዋናተኞች አለቃ ግን በጥበቡ መቅዘፍያ አሻገረኝ÷ የጠላት ቅጥረኞች ተነሡብኝ በጽድቅ የሚፈርድ እርሱ በቃሉ ሰይፍ ወጋቸው÷ እባብ መርዝን የተሞላ ምላሱን አውለበለበ እግዚአብሔር ግን በአገዛዙ ልጓም ለጐመው፡፡ ስላደረገልኝ ሁሉ ለእግዚአብሔር ምን እከፍለዋለሁ፡፡ ከእንግዲህስ እግዚአብሔርን ዘወትር አየዋለሁ፡ ሁልጊዜ በፊቴ ነው እንዳልታወክ እርሱ በቀኜ ነውና ስለዚህም ልቤ ደስ ተሰኘ አንደበቴም ሐሤትን አደረገ እል ዘንድ ይገባኛል፡፡ መዝ ፲፰÷፰-፱

፫ ዳግመኛም ነፍሴ ለምን ታዝኛለሽ ለምንስ ታውኪኛለሽ በእግዚአብሔር እመኚ በፊቴ ለሚያድነኝ እገዛለት ዘንድ እርሱ አምላኬ ነው እል ዘንድ ይገባኛል፡፡ሁለተኛም እግዚአብሔር ያበራልኛል ያድነኛልም ምን ያስፈራኛል እግዚአብሔር ለሕይወቴ መታመኛዋ ነው ምን

ርሀኒ፡፡እግዚአብሔር ምእመና ለሕይወትየ ወም ንትኑ ያደነግፀኒ፡፡ወይእዜኒ ክሥት እግዚኦ እዝነ ልብየ ከመ እንግር ስብሐቲከ ዘከመ ተሰ ባሕከ በአፈ ሕፃናት ወከመ አብስራ ለኢየ ሩሳሌም በቃለ ነቢያት እንዘ እብል ብስራትኪ ብስራትኪ ኢየሩሳሌም ናሁ መጽአ ንቤኪ ዘበ እንቲአሁ ይቤሉ መዘምራን ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር፡፡ባረክናክሙ በስመ እግ ዚአብሔር እግዚአብሔር እግዚእ አስተርአየ ለነ፡፡ብስራትኪ ብስራትኪ ኢየሩሳሌም ናሁ በጽሐ ብርሃንኪ ዘበእንቲአሁ ይቤ ኢሳይያስ፡፡ አብርሂ አብርሂ ኢየሩሳሌም በጽሐ ብርሃንኪ ወስብሐተ እግዚአብሔር ሠረቀ ላዕሌኪ፡፡ ብስ ራትኪ ብስራትኪ ኢየሩሳሌም ናሁ መጽአ ንጉሥኪ ዘበእንቲአሁ ተነበየ ዘካርያስ ወይቤ ትፈሥሒ ወለተ ጽዮን ወተሐሠዪ ወለተ ኢየ ሩሳሌም፡፡ናሁ ይመጽእ ንጉሥኪ ጻድቅ ወየዋ ህ ዘይጼዓን ዲበ አድግ ወዲበ ዕዋለ አድግ፡፡ መዝ ፻፳፩፥፩ ፤፵፯፥፭ ኢሳ ፷፪፥፪ ዘካ ፱፥፱

፬ ብስራትኪ ብስራትኪ ኢየሩሳሌም ሀገሮሙ ለነቢያት እስመ እግዚአ ነቢያት ሐወፀኪ ከመ ይፈጽም ቃለ ተነብዮቶሙ፡ብስራትኪ ብስራ ትኪ ኢየሩሳሌም ሀገረ ሙላዶሙ ለሐዋርያት እስመ ኢየሱስ ክርስቶስ መጽአ ኀቤኪ በሥጋ ሰብእ፡፡ ወሐዋርያትኒ የዱኪ እንዘ ይብሉ ሆሳዕና ለወልደ ዳዊት ለወልደ ዳዊት፡እስመ ኩሎሙ ነቢያትኒ ወሐዋርያትኒ ዜነዉ ልደቶ ለክርስቶስ ከመ እምዘርአ ዳዊት ውእቱ፡፡ በእፎኬ ተስእሎሙ ለፈሪሳውያን ወይቤሎሙ ምንተ ትብሉ በእንተ ክርስቶስ፡ ወልደ መኑ ውእቱ ክርስቶስ፡፡ ወይቤልዎ ወልደ ዳዊት፡፡ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ እፎኬ ለሊሁ ዳዊት ይቤ በመንፈስቅዱስ ይቤሎ እግዚእ ለእግዚእየ ንበር በየማንየ እስከ አገብኦሙ ለጸ ላዕትከ ታሕተ መከየደ እገሪከ፡፡ዘለሊሁ እንከ ዳዊት እግዚእየ ይቤሎ በመንፈስ እፎ እንከ ይከውኖ ወልዶ፡፡ወአልቦ ዘክህለ አውሥኦቶ ወተሰጥዎቶ ቃለ፡፡ምንተ እንከ ንብል በእንተ ዝ ቃለ እግዚእ ክሕደኑ ንብል ልደቶ ዘእም ድንግል እስመ ለማርያምስ አእመርናሃ ጥዩቀ ከመ እምዘርአ ዳዊት ተወልደ፡አኮኑ ውእቱ ይቤ እስመ ወልደ እግዚአብሔር ወልደ እጓለ እመሕያው ውእቱ፡፡ መዝ፻፱፥፩ ማቴ፳፪፥፵፩-፵፮ ዮሐ፯፥፵፪

፭ ወካዕበ ይቤ አሌ ሎቱ ለዘእምኔሁ ይትሜጠውዎ ለወልደ እጓለ እመሕያው፡፡ ወዓዲ ይቤ ወልደ እጓለ እመሕያውሰ የሐውር በከመ

ያስደነግጠኛል እል ዘንድ ይገባኛል፡፡ አሁንም አቤቱ በሕፃናት አንደበት እንደተመሰገንህ ምስጋናህን እናገር ዘንድ ኢየሩሳሌምንም በነቢ ያት ቃል የምሥራች የምሥራች ኢየሩሳሌም እነሆ አመስጋኞች ስለርሱ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተመሰገነ ነው፡ በእግዚአብሔር ስም መረቅናችሁ ጌታ እግዚአብሔር ተገለጠልን፤ ኢየሩሳሌም ሆይ የምሥራች የምሥራች እነሆ ኢሳይያስ ስለርሱ ኢየሩሳሌም ሆይ አብሪ አብ ሪ፡ የእግዚአብሔር ክብር በአንቺ ላይ ተገለጠ ብሎ የተናገረለት ብርሃንሽ ደረሰ፤ ኢየሩሳሌም ሆይ የምሥራች የምሥራች እነሆ ዘካርያስ ስለርሱ የጽዮን ሴት ልጅ ሆይ ደስ ይበልሽ የኢየሩሳሌም ሴት ልጅ ሆይ ሐሤትን አድርጊ እነሆ ጻድቅና የዋህ ንጉሥሽ በአህያይቱና በውርንጭላዋ ላይ ተጭኖ ወደ አንቺ ይመጣ ልና ብሎ የተናገረለት ንጉሥ መጣ፡፡ መዝ ፻፳፩፥፩ ፤፵፯፥፭ ኢሳ ፷፪፥፪ ዘካ ፱፥፱

፬ የነቢያት ሀገራቸው ኢየሩሳሌም ሆይ የምሥራች የምሥራች የነቢያት ጌታ የትንቢት ቃላቸውን ይፈጽም ዘንድ ጐብኝቶሻ ልና፡፡ የነቢያት የትውልድ ሀገራቸው ኢየሩ ሳሌም ሆይ የምሥራች የምስራች ኢየሱስ ክርስ ቶስ በሰው ሥጋ ወደአንቺ መጥቷልና፡፡ ሐዋ ርያት ሆሣዕና በአርያም ሆሣዕና በአርያም ሆሣ ዕና ለዳዊት ልጅ እያሉ ዞሩሽ ነቢያትና ሐዋ ርያት ሁላቸው ልደቱ ከዳዊት ወገን እንደሆነ ተናግረዋልና፡፡ ፈሪሳውያን ስለ ክርስቶስ ምን ትላላችሁ ክርስቶስ የማን ልጅ ነው ብሎ ጠየ ቃቸው፡ እነርሱም የዳዊት ልጅ ነው አሉት፥ ጌታ ኢየሱስም እርሱ ራሱ ዳዊት እንዴት በ መንፈስቅዱስ ጌታ ጌታዬን ጠላቶችህን ከእግርህ መረገጫ በታች እስካስገዛልህ ድረስ በቀኜ ተቀ መጥ አለው፥ እንግዲህ ዳዊት ራሱ በመንፈስ ጌታዬ አለው እንዴት ልጁ ይሆናል አላቸው፥ ቃል ሊመልስለት የተቻለው የለም፡፡ ስለዚህ የጌታ ቃል እንግዲህ ምን እንላለን ከድንግል መወለዱን ካደ እንላለንን ማርያምን ከዳዊት ወገን እንደተወለደች በጉላ በተረዳ ነገር ዐው ቀናታልና፡፡ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ነው ብሎ ተናግሮ የለምን፡፡ መዝ፻፱፥፩ ማቴ፳፪፥፵፩-፵፮ ዮሐ፯፥፵፪

፭ ዳግመኛም የሰው ልጅ አልፎ ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ወዮለት አለ፡፡ ከእን ደገናም የሰው ልጅስ እንደተጻፈ ይሄዳል

ጽሑፍ፡፡ወካዕበ ይቤ በእንተ ዕርገቱ ትሬእ ይዎ ለወልደ እጓለ እመሕያው እንዘ የዐርግ ኀበ ሀሎ ቀዲሙ፡፡ወካዕበ ይቤ አልቦ ዘዐርገ ውስተ ሰማይ ዘእንበለ ዘወረደ እምሰማይ ወል ደ እጓለ እመሕያው፡፡ርኢኬ ዘከመ ይኖልቁ ርደተ መለኮት ለዘኢወረደ ሥጋ እምሰማይ፡፡ ወከማሁ ይትኖለቁ ሎቱ ሐሳበ ሕማማቲሁ ለትስብእት ኀበ መለኮት እንዘ መለኮትሰ ኢይ ትለከፍ ለሕማማተ ሥጋ፡፡በከመ ተኖለቈ ር ደተ መለኮት ኀበ ትስብእት እንዘ ትስብእትሰ ዓዲሃ ኢነበረት ውስተ ሰማይ፡፡አላ ከመ ያስ ተዛውጋ ምስለ መለኮት ይቤ ዘንተ፡፡

፮ በእንተ ምጽአቱሂ ይቤ ትሬእይዎ ለወልደ እጓለ እመሕያው እንዘ ይመጽእ በደ መና ሰማይ ወይነብር በየማነ ኃይል፡፡ኃይለ ይሰምዩ ለአቡሁ በዝ ከመ ይመጽእ በየማነ ወላዲሁ እንዘ ይኤምር ይቤ ዘንተ፡፡እስመ ኀበ ሰመየ ርእሶ ወልደ እጓለ እመሕያው ይሰሚ ርእሶ፡፡ወብሂለ ወልደ እግዚአብሔርሰ ዘእን በለ በበንስቲት ከመ ይንጦላዕ ህላዌሁ በአመ ሥጥሮ እምኀሊና አይሁድ ከመ ኢይትአመር ሎሙ እስመ ይትገሀ ለሕማማተ መስቀል በከ መ አብሖ ለይሁዳ ወይቤሎ ዘትገብር እንከ ፍጡነ ግበር፡፡ ማቴ፳፮+፴

፯ ወእመሰ ኢኀፈረ ብሂለ ወልደ እጓለ እመሕያው በእንተ ርእሱ እፎኬ ኢኀፈረ ብሂለ ወልደ ዳዊት፡፡እስመ እም እጓለ እመሕያውሰ ቦ ፅኑስ ወቦ ዝለጉስ ቦ ዕውር ወቦ ፅቡስ ወቦ ጥዑይ ወቦ ድውይ ወቦ ባዕል ወቦ ነዳይ ቦ ሕሡም ወቦ ቅድው ቦ አይሁዳዊ ወቦ አረ ማዊ ቦ ጻድቅ ወቦ ኀጥእ ቦ ጠቢብ ወቦ አብድ፡፡

፰ ወዳዊትሰ ንጉሠ እስራኤል ውእቱ በዕበየ መንግሥቱ ወፍቁረ እግዚአብሔር ውእ ቱ በተነብዮቱ፡ዘበእንቲአሁ ይቤ በነቢይ ረከ ብክዎ ለዳዊት ገብርየ ብእሴ ምእመነ ዘከመ ልብየ፡ወካዕበ ይቤ ወበህየ አበቊል ቀርነ ለዳ ዊት፡ ወአስተዴሉ ማኅቶተ ለመሲሒየ፡፡ወእ ለብሶሙ ኀፍረተ ለጸላእቱ፡ቦቱ ይፈሪ ቅድሳ ትየ፡፡ወለሊሁኒ ዳዊት ይቤ እግዚአብሔር ይቤለኒ ወልድየ አንተ ወአነ ዮም ወለድኩከ፡፡ እመሰ የኀፍር ብሂለ ወልደ ዳዊት እምኀፈረ ፈድፋደ ብሂለ ወልደ እጓለ እመሕያው፡፡ መዝ ፪+፯፣፻፴፯+፲፯

፱ ወዘይቤሎሙሰ ለፈሪሳውያን ዘለሊሁ ዳዊት እግዚእየ ይቤሎ እፎ እንከ ይከውኖ ወልዶ፡፡እንዘ ያሌዕላ መድኀነ ለትስብእት

አለ፡፡ ሁለተኛም ስለ ዕርገቱ የሰውን ልጅ ቀድሞ ወደ ነበረበት ሲያርግ ታዩታላችሁ አለ፡፡ ዳግመ ኛም ከሰማይ ከወረደው ከሰው ልጅ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ የለም አለ፡፡ከሰማይ ላልወረደ ለሥጋ የመለኮትን መውረድ ሲቈጥር እይ፡፡ የመለኮት መውረድ ለሰውነት እንደተቈጠረ እንዲሁ መለኮት በሥጋ መከራዎች የማይነካ ሲሆን የትስብእት የሕማማቱ ቁጥር ለመለኮት ተቈጠረለት፥ ትስብእት ግን ገና በሰማይ አልተቀመጠችም ከመለኮት ጋር ያዛምዳት ዘንድ ይህን ተናገረ እንጂ፡፡

ማቴ፳፮+፳፬ ዮሐ፫+፲፫

፮ ስለ መምጣቱም የሰውን ልጅ በኃይል ቀኝ ተቀምጦ በሰማይ ደመና ሲመጣ ታዩታላችሁ አለ፡፡ በዚህ አባቱን ኃይል አለው በወለደው ቀኝ ሆኖ እንደሚመጣ ሲያመለክት ይህን ተናገረ ራሱን ሲጠራ የሰው ልጅ ብሎ ይጠራልና፥ አልፎ አልፎ የእግዚአብሔር ልጅ ማለቱም ይሁዳን የምታደርገውን እንግዲህ ፈጥነህ አድርግ ብሎ እንደፈቀደለት እንዳይ ገለጥላቸው ከአይሁድ ኀሊና የረቀቀ በማድረግ ህልውናው እንዲከለል ነው፡፡ ማቴ፳፮+፴

፯ ስለ ራሱ የሰው ልጅ ለማለት ካላፈረ የዳዊት ልጅ ለማለት እንደምን ያፍራል፡፡ ከሰው ልጅስ መካከል የተቸገረ አለ፥ ልምሾም አለ፥ የታወረ አለ፥ ደካማም አለ፥ ጤነኛ አለ፥ በደዌ የተያዘም አለ፥ ባለጠጋ አለ፥ ችግረኛም አለ፥ መልከ ክፉ አለ፥መልከመልካምም አለ፥አይሁዳ ዊ አለ፥ የአሕዛብም ወገን አለ፥ጻድቅ አለ ኃጢ አተኛም አለ ጥበበኛም አለ፥ ሰነፍም አለ፡፡

፰ ዳዊትስ በመንግሥቱ ክብር የእስራኤል ንጉሥ ነው ትንቢት በመናገሩም የእግዚአብሔር ወዳጅ ነው፡ ነቢይ ስለርሱ እንደልቤ የታመነ ሰው ባሪያዬ ዳዊትን አገኘሁት ብሎ የተናገረለት፡፡ ሁለተኛም በዚህም ለዳዊት ቀንድን አበቅላለሁ ለቀባሁትም መብራትን አዘጋጃላሁ ጠላቶቹን ግን እፍረትን አለብሳቸ ዋለሁ በርሱም ቅድስናዬ ያፈራል አለ፡፡ ዳዊትም ራሱ እግዚአብሔር አንተ ልጄ ነህ እኔም ዛሬ ወለድሁህ አለኝ አለ፡፡ የዳዊት ልጅ ለማለት ቢያፍር የሰው ልጅ ለማለት አብዝቶ ባፈረ ነበር፡፡ መዝ ፪+፯፣፻፴፯+፲፯

፱ ለፈሪሳውያን ዳዊት ራሱ ጌታዬ አለው እንግዲህ እንዴት ልጁ ይሆናል ያላቸው ግን መድኃኒታችን በመለኮት መዋሐድ ላማረ

በጽምረት መለኮት ከመ ትኩን አሐደ ለሠናይ አምልኮ ከመ ኢየኀልይዋ ኀበ ክልዔ ግዕዝ ዘእንበለ ኀበ አሐዱ አካል ወአሐዱ ራእይ። እስመ ፈሪሳውያንሰ ይብልዎ ለክርስቶስ ወልደ ዳዊት። ይሜህሩ ብህኑነ ሥጋዌ ዘእንበለ ጽምረተ መለኮት።ወኢአምኑ ከመ ወልደ እግዚአብሔር ተሠጊዎ እምወለተ ዳዊት ይሰመይ ወልደ ዳዊት።ወበእንተዝ መተረ ሥርወ ኀሊናሆሙ በመጥባሕተ ቃሉ ከመ ኢየኀልይዎ ከመ እምዘርአ ብእሲ ተወልደ።እስመ እሙንቱ አምሰልዎ ከመ ወልደ ዮሴፍ ውእቱ።እስመ ይቤሉ ዘለሊነ ነአምር አባሁ ወእሞ እፎ እንከ ይብለነ እምሰማይ ወረድኩ። ማቴ፲፫፥፶፭

፲ ወበዝ ቃል ካዕበ ገዘረ ቊልፈተ ልቦሙ ሶበ ይቤ ዘለሊሁ ዳዊት እግዚእየ ይቤሎ እፎ እንከ ይከውኖ ወልዶ። ወለሥጋሰ ዘነሥአ እምወለተ ዳዊት አስተዋህዳ ምስለ መለኮቱ ዘበአሐዱ አካል ከመ ኢይትሌለይ መለኮቃ ለከዊነ እግዚአብሔር።ሶበ ይቤሎ ለፊ ልጶስ ዘርእየ ኪያየ ርእዮ ለአቡየ፡እስመ ለዘር እየ ትስብእቶ ኖለቈ ሎቱ ከመ ዘርእየ መለኮተ አቡሁ፡ወበዝ መጥባሕተ ቃል መተረ ልሳኖ ለንስጥሮስ ዘይቤሎ ከመ አሐዱ እምነቢ ያት።ወበዝ መጥባሕተ ቃል መተረ ልሳኖ ለ ልዮን ዘይቤ የኀጽጽ ትስብእት እመለኮት እምድኅረ አሐዱ ከዊን።መጥባሕተ ቃል መተረ ልሳኖሙ ለማኅበረ ኬልቄዶን እለ ይቤ ሉ መለኮት ወትስብእት በክልዔ ፍና ወበክ ልዔ ሥርዓት።ዘይደሉ ለመለኮት ገብረ መለ ኮት ወዘይደሉ ለትስብእት ገብረ ትስብእት። ወበዝ ቃል መተረ ልሳኖ ለፍልብያኖስ ዘይቤ ክልዔ ገጸ መለኮቱ ወትስብእቱ ለመድኃኒነ። ዮሐ ፲፬፥፱

፲፩ ወእምይእዜሰ ንጸውዖ ለያዕቆብ እስራኤል ከመ ይንግረነ ቡራኬያቲሁ ዘይቤ በእንተ ይሁዳ።ይሁዳ ሰብሑከ አኀዊከ እዴ ከ ላዕለ ዘባኖሙ ለጸላዕትከ ይሰግዱ ለከ ደቂ ቀ እቱከ። ይሁዳ እጓለ አንበሳ እምኀዝአትከ ዕርግ። ወልድየ ሰከብከ ወኖምከ ከመ አንበሳ ወከመ እጓለ አንበሳ አልቦ ዘያነቅህከ። ወኢይ ጠፍእ ምልክና እምይሁዳ ወምስፍና እምአባ ሉ። እስከ አመ ይረከብ ዘፅኑሕ ሎቱ ውእቱ ተስፋሆሙ ለአሕዛብ። የአሥር ውስተ ዓጸደ ወይን ዕዋሎ ወበዕፀ ዘይት አድጎ። የሐፅብ በወይን አልባሲሁ ወበደመ አስካል ሰንዱኖ። ፍሡሐት እምወይን አዕይንቲሁ ወጸዕዳ ከመ

አምልኮ በአንድ አካልና በአንድ ኀብረ መልክዕ እንጂ በሁለት ጠባይ እንዳያስቡት አንድ ትሆን ዘንድ ትስብእትን ከፍ ከፍ ሲያደርጋት ነው እንጂ። ፈሪሳውያንስ ክርስቶስን የዳዊት ልጅ ይሉታል ያለ መለኮት መዋሐድ የተበተነ ሰው ነትን ያስተምራሉ። የእግዚአብሔር ልጅ ከዳዊት ሴት ልጅ ሰው ሆኖ ተወልዶ የዳዊት ልጅ እንደሚባል አያምኑም። ስለዚህም የዮሴፍ ልጅ እንደሆነ አስመስለውታልና ከወንድ ዘር እን ደተወለደ እንዳያስቡት በቃሉ ጕራዴ የአሳ ባቸውን ሥር ቆረጠ። እኛ አባቱንና እናቱን የም ናውቃቸውን እንግዲህ እንዴት ከሰማይ ወረድሁ ይለናል ብለዋልና።
ማቴ፲፫፥፶፭

፲ በዚህም ቃል ሁለተኛ ዳዊት ራሱ ጌታዬ አለው እንግዲህ እንዴት ልጁ ይሆናል ባለ ጊዜ የልባቸውን ሽለፈት ገረዘ፥ ከዳዊት ሴት ልጅ የነሣውን ሥጋ ግን በአንድ አካል ካለ ከመለኮት ጋር አዋሀዳት እንዳትለይ እግዚአብሔርን ወደመሆን ከፍ አደረጋት። ለፊልጶስ እኔን ያየ አባቴን አየው ባለው ጊዜ ሰውነቱን ላየ የአባቱን መለኮት እንዳየ ቆጥ ሮለታልና። በዚህም ቃል ጕራዴነት የዮሴፍ ልጅ እንደሆነ የሚያስቡ የጸፎችና የፈሪሳውያንን የአሳባቸውን ሽለፈት አስወገደ። በዚህም ቃል ጕራዴነት ከነቢያት አንዱ ነው ያለውን የንስ ጥሮስን ምላስ ቆረጠ፥ በዚህም ቃል ስለትነት ከተዋሕዶ በኋላ ሰውነት ከመለኮት ያንሣል ያለ የልዮንን ምላስ ቆረጠ። በዚህም ቃል ሰይፍነት መለኮትና ሰውነት በሁለት መንገድ በሁለት ሥርዓት ናቸው፥ ለመለኮት የሚገባውን መለኮት ሠራ ለሥጋም የሚገባውን ሥጋ አደረገ ያሉ የኬልቄዶንን ማኅበረተኞች ምላሳቸውን ቆረጠ፥ በዚህም ቃል የመድኃኒታችን የመለኮቱና የሰውነ ቱ መልክ ሁለት ነው ያለ የፍላብያኖስን ምላስ ቆረጠ። ዮሐ ፲፬፥፱

፲፩ አሁንስ ስለ ይሁዳ የተናገረውን ምርቃቶቹን ይናገር ዘንድ እስራኤል የተባለ ያዕቆብን እንጥራው። ይሁዳ ሆይ ወንድሞችህ ያከብሩህ እጅህ በጠላቶችህ ጀርባ ላይ ነው የወንድሞችህ ልጆች ይሰግዱልሀል ይሁዳ የአን በሳ ደቦል ነው ከአደንህ ውጣ ልጄ ሆይ እንደ አንበሳ ተኛህ አንቀላፋህም እንደ አንበሳም ደቦል የሚቀሰቅስህ የለም መንግሥት ከይሁዳ አይወ ጣም ገዢነትም ከወገኖቹ ገዢውን እስኪያገኝ ድረስ እርሱ የአሕዛብ ተስፋቸው ነው፡ ውርን ጭላውን በወይኑ አፀድ ያሥራል አህያውንም በወይራ እንጨት ልብሶቹን በወይን ያጥባል በፍታውንም በፍሬ ደም፤ ዓይኖቹ ከወይን ይልቅ ደስ ያሰኛሉ ጥርሶቹም እንደ ወተት ነጭ

ሐሊብ አስናኒሁ፡፡ዮም ተፈጸመ ቃል ዝ ትን ቢት ዘአቡነ ያዕቆብ ዘይቤ በእንተ ይሁዳ ወፍጻሜ ነገሩሰ በኢየሱስ ክርስቶስ ይትፌጸ ም፡በከመ ይቤሎ ለዳን ዳን ይኴንን ሕዝቦ ከመ አሐቲ እምነገደ እስራኤል ኮኖ ለዳን አርዌ ምድር ዘይጸንሖ ወይነስኮ ሰኰናሁ ለፈ ረስ ወይወድቅ ዘይጼዓኖ ድኅሬሁ ወይጸንሕ ከመ ያድኅኖ እግዚአብሔር ወእግዚአብሔር ይጼንዖ፡፡ዘፍ ፵፱፥፲፮-፲፯

፲፪ ዳን ይኴንን ሕዝቦ ከመ አሐቲ እም ነገደ እስራኤል ይተረጐም በመንግሥተ ሐሳዌ መሲሕ፡፡እስመ ሙሴኒ ይቤ በቡራኬ ያቲሁ ዳን እጓለ አንበሳ ወይሰርር እምባሳን፡፡ ዘንተ ይቤ በእንተ ትግርምተ መንግሥቱ ሰይ ጣናዊት፡፡እስመ ብሂለ አንበሳ ኀበ ክልኤ ይተ ረጐም ኀበ መንግሥተ ኢየሱስ ክስቶስ ዘበኃ ይለ መንፈስቅዱስ እስመ ይገብር መንክራተ በከመ አቡሁ ይገብር ለመድኃኒተ ዓለም፡፡ ወካዕበ ይተረጐም ኀበ መንግሥተ ሐሳዌ መሲሕ ዘይገብር መንክራተ በኃይለ አቡሁ ሰይጣን ለአስሕቶ ዓለም፡፡

፲፫ በእንተ መንግሥተ ኢየሱስ ክርስቶስ ይቤ ያዕቆብ ይሁዳ እጓለ አንበሳ ሰከብከ ወኖምከ ከመ አንበሳ ወከመ እጓለ አንበሳ አልቦ ዘያነቅህከ፡፡ወበእንተሐሳዌ መሲ ሕ ይቤ ሙሴ ዳን አንበሳ ወይሰርር እምባሳን ፡፡በእንተ መንግሥተ ኢየሱስ ክርስቶስ ካዕበ ይቤ ዮሐንስ አቡቀለምሲስ ወይቤለኒ መልአክ ኢትብኪ ናሁ ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዘእምውስተ ሥርዉ ለዳዊት፡፡ወበእንተ መንግ ሥተ ሐሳዌ መሲሕኒ ይቤ ጴጥሮስ ጥበቡ እንከ ወአጥብቡ ልበክሙ እስመ ጸላኢክሙ ጋኔን ከመ አንበሳ ይጥሕር ወየኃሥሥ ዘይው ኅጥ፡፡ወበእንተ መንግሥተ ኢየሱስ ክርስቶስ ይቤ ያዕቆብ ኢይጠፍእ ምልክና እም ይሁዳ ወምስፍና እም አባሉ እስመ አመ ይረከብ ዘጽ ኑሕ ሎቱ ውእቱ ተስፋሆሙ ለአሕዛብ፡፡

፲፬ በእንተ መንግሥተ ሐሳዌ መሲሕ ይቤ ኮኖ ለዳን አርዌ ምድር ዘይፀንሖ በውስ ተ ፍኖት ወይነስከ ሰኰናሁ ለፈረስ ወይወድ ቅ ዘይጼዓኖ ወእግዚአብሔር ይጼንዖ እስመ ኵሎ ዘያፈቅር ይፀንሖ ለፍቁሩ ውስቴ ፍኖት ከመ ይትቀበሎ በፍስሓ እስመ የአምር ከመ ይገብር ሎቱ ፈቃዶ፡፡ እስመ አልቦ ዘያፈቅር ሰይጣን ከመ ይሁዳ ሰያጤ እግዚኡ

ናቸው፡፡ ስለ ይሁዳ የተናገረው የአባታችን የያዕቆብ ትንቢት ቃል አሁን ተፈጸመ፡፡ የነገሩ ፍጻሜ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጸመ፡፡ ዳንን ዳን ሕዝቡን ከእስራኤል ነገዶች እንደ አንዲቱ ይገዛል ዳንን እባብ ይጠብቀዋል የፈረሱንም ሰኰናውን ይነክሰዋል የተጫነበትም ከኋላው ይወድቃል እግዚአብሔርም ያድነው ዘንድ ይጠብቀዋል እንዳለው፡፡ ዘፍ ፵፱፥፲፮-፲፯

፲፪ ዳን ከእስራኤል ነገዶች እንደ አንዲቱ ሕዝቡን ይገዛል ያለው በሐሳዌ መሲሕ መንግሥት ይተረጐማል፡፡ ሙሴም በምርቃቶቹ ዳን የአንበሳ ደቦል ነው ከባሳንም ይበርራል ብሏልና፥ ስለ ሰይጣናዊት መንግሥቱ መስፋፋት ይህን ተናገረ፡፡ አንበሳ ማለት በሁለት ይተረጐ ማልና በመንፈስቅዱስ ኃይል በሚሆን በኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት ዓለምን ለማዳን አባቱ እንደሚያደርግ ድንቆችን ያደርጋልና፡፡ ሁለተኛም ዓለምን ለማሳት በአባቱ በሰይጣን ኃይል ድንቆችን በሚያደርግ በሐሳዌ መሢሕ መንግ ሥት ይተረጐማል፡፡

፲፫ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥትም ያዕቆብ ይሁዳ የአንበሳ ደቦል እንደ አንበሳ ተኛህ አንቀላፋህም እንደ አንበሳም ደቦል የሚቀሰቅስህ የለም አለ፡፡ ስለ ሐሳዌ መሲሕም ሙሴ ዳን አንበሳ ነው ከባሳንም ይበርራል አለ፡፡ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥትም ሁለተኛ ዮሐንስ አቡቀለምሲስ መልአኩም አታልቅስ እነሆ ከዳዊት ሥር ከይሁዳ ወገን የሆነ አንበሳ አቸንፏል አለኝ አለ፡፡ ስለ ሐሳዊ መንግሥትም ጴጥሮስ እንግዲህስ ጥበበኞች ሁኑ ልባችሁንም ጥበበኛ አድርጉ ጠላታችሁ ጋኔን የሚውጠውን ሽቶ እንደ አንበሳ ይጮሀልና አለ፡፡ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስም መንግሥት ያዕቆብ መንግሥት ከይሁዳ አይወጣም ግዛትም ከወገኖቹ፥ ገዢው\ን እስኪያገኝ ድረስ እርሱ የአሕዛብ ተስፋቸው ነው አለ፡፡

፲፬ ስለ ሐሳዌ መሲሕ መንግሥትም ዳንን የምድር እባብ በመንገድ ይጠብቀዋል የፈረሱንም ሰኰና ይነክሳል የተጫነበትም ይወድቃል እግዚአብሔርም ይጠብቀዋል ሁሉን የሚወድ እርሱ ወዳጁን በደስታ ይቀበለው ዘንድ በመንገድ ይጠብቀዋል፡፡ ፈቃዱን እንደሚያ ደርግለት ያውቃልና፡፡ ጌታውን እንደሸጠ እንደ ይሁዳ እኔ ክርስቶስ ነኝ እንደሚልም እንደ ሐሳዌ መሲሕ ሰይጣን የሚወደው የለምና

ወከመ ሐሳዌ መሲሕ ዘይቤ አነ ውእቱ ክርስቶስ እስመ ከልዔሆሙ እምነገደ ዳን፡፡ውእቱ ፀንሐሙ በፍኖተ ኢየሩሳሌም ከመ ይግበሩ ሎቱ ፈቃዶ፡፡ለይሁዳ ፀንሖ ኀበ መርኅበ ኢየሩሳሌም ከመ ይግበር ሎቱ ኪዳነ ምስለ ሊቃነ ካህናት ውእቶሙኒ ከመ የሀብዎ ሠላሳ ብሩረ በሰቅል ቅዱስ ወውእቱኒ ከመ ያግብኦ ሎሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡፡ ዕፁብኬ አፍቅሮ ንዋይ እምኵሉን ኃጣውእ እስመ ቀዲሙኒ ሠራቄ ብሩር ውእቱ ዘውስተ ቀምጠራ ዘአስከሬነ እግዚእ፡ወበእንተ ማርያሂ ይቤ ሶበ አምጽአት ዕፍረተ ዘአልባስጥሮስ በቢሬሌ ወሶጠት ዲበ ርእሱ ለእግዚእ ኢየሱስ ወመልአ ቤተ መዓዛሁ ለውእቱ ዕፍረት፡፡ይቤ ለምንት ኢሜጥዎ ለዝንቱ ዕፍረት በሠለስቱ ምእት ዲናር ከመ የሀብዎሙ ለነዳያን፡፡ወበእንተዝ ዘለፎ ወንጌላዊ ወይቤ አኮ በምሒረ ነዳይ ዘይቤ ዘንተ እስመ ሠራቂ ውእቱ ወየዐቅብ ወርቀ መባአ ወይነሥእ እምዘ ውስቴቱ፡፡ወበዝኒ ኵሉ ኢጸገቦ ፍቅረ ንዋይ ደፈረ እስከ ለሜጠ እግዚኡ፡፡ ዮሐ ፲፪፥፩-፰

ሁለቱም ከዳን ወገን ናቸው ፈቃዱን እንዲያደርጉለት በኢየሩሳሌም ጉዳና ቆያቸው፡፡ ይሁዳን ከካህናት አለቆች ጋር ስምምነትን እንዲያደርግለት እነርሱም በቅዱሱ ሚዛን ሠላሳ ብር ይሰጡት ዘንድ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስን አሳልፎ እንዲሰጣቸው በኢየሩሳሌም አደባባይ ቆየው፡፡ ከኃጢአቶች ሁላቸው ገንዘብ መውደድ ምንኛ ጭንቅ ነው፥ ቀድሞም በጌታው ሣጥን ሙዳይ ውስጥ ያለውን ብር የሚሠርቅ ነበረ፡፡ ስለ ማርያም የአልባስጥሮስ ሽቱ በብልቃጥ አምጥታ በጌታ ኢየሱስ ራስ ላይ ባፈሰሰችው ጊዜ የሽቱውም መዓዛ ቤቱን በመላው ጊዜ ለችግረኞች ይሰጥ ዘንድ ይህ ሽቱ ለምን በሦስት መቶ ዲናር አልተሸጠም አለ፡ ስለዚህም ነገር ወንጌላዊ ይህን የተናገረው ለችግረኞች በመራራት አይደለም ሌባ ነውና የሚገባውን ገንዘብ ይጠብቅ በወስጡ ካለውም ይወስድ ነበርና ብሎ ዘለፈው፡፡ በዚህ ሁሉ ገንዘብን መውደድ አልጠግብ ብሎ ጌታውን እስከመሸጥ ድረስ ተደፋፈረ፡፡ ዮሐ ፲፪፥፩-፰

፲፭ ወለሐሳዌ ወሲሕኒ ፀንሖ እንከ አርዌ ምድር ኀበ ኖኅተ ኢየሩሳሌም ወደየ ሕምዘ ውስተ ልቡ ከመ ኢይፍርሆ ለእግዚአ ብሔር ወከመ ኢይኀፈር ሰብአ ከመ ይቤ እግ ዚእነ በወንጌል፡፡ሀሎ አሐዱ መኰንን በአሐቲ ሀገር ዘኢይፈርሆ ለእግዚአብሔር ወኢየኀፍር ሰብአ፡፡ወሀለወት በይእቲ ሀገር አሐቲ እቤር ብእሲት ወትመጽእ ኀቤሁ ወትብሎ ኰንነኒ እምዕድውየ አበያ ወአጕንደያ፡፡ወእምዝ ኀለየ ወይቤ እመሰ ኢይፈርሆ ለእግዚአብሔር ወኢየኀፍር ሰብአ እኰንና እንከ ለዛቲ እቤር ከመ ኢታንጥየኒ ወከመ ኢትምጻእ ዘልፈ ወኢ ታስርሐኒ፡፡ወይቤሎሙ እግዚእነ ስምዑ ዘይቤ መኰንነ ዐመፃ እግዚአብሔርኑ እንከ ኢይፈ ትሕ ለኅሩያኒሁ ለእለ ይግዕሩ ኀቤሁ መዐል ወሌሊተ፡፡መኰንነ ዓመፃሰ ዘኢይፈርሀ እግዚ አብሔር ወኢየኃፍር ሰብአ ሐሳዌ መሲሕ ውእቱ ዘኢይፈርሆ ለእግዚአብሔር እንዘ ይሰሚ ርእሶ በስመ ወልዱ ወኢየኃፍሮሙ ለእጓለ እመሕያው እንዘ ያነብር ጣዖተ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር ወይኤዝዝ ከመ ይስግዱ ለምስሉ ለቀዳማዊ አርዌ፡፡ ዮሐ ፲፪፥፩-፰

፲፭ ሐሳዌ መሲሕንም እንግዲህ እባብ በኢየሩሳሌም በር ጠበቀው እግዚአ ብሔርን እንዳይፈራው ሰውንም እንዳያፍር መርዝ በልቡ ጨመረ፡፡ ጌታችን በወንጌል በአንዲት ሀገር እግዚአብሔርን የማይፈራው ሰውንም የማያፍር አንድ ዳኛ ነበረ፥ በዚያችም ሀገር አንዲት አሮጊት ሴት ነበረች ወደርሱም እየመጣች ከባለ ጋራዬ ፍረድልኝ ትለው ነበር፥ እርሱ ግን አልፈረድላት አለ አዘገያትም፡፡ ከዚ ህም በኋላ እግዚአብሔርን ባልፈራ ሰውንም ባላፍር እንዳትጨቀጭቀኝ ዘወትርም እየመጣች እንዳታደክመኝ ይህቺን አሮጊት ልፍረድላት ብሎ አሰበ፡፡ ጌታችንም ዓመፀኛው ዳኛ ያለውን ስሙ እንግዲህ እግዚአብሔር በቀንና በሌሊት ወደርሱ ለሚጮሁት ለምርጦቹ አይፈርድምን አላቸው፡፡ እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰውንም የማያፍር ዓመፀኛ ዳኛስ ራሱን በልጁ ስም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ሲጠራ እግዚአብሔርን ያልፈራው ጣዖትንም ሲያስቀምጥ የሰው ልጆችን ያላፈራቸው ሐሳዌ መሲሕ ነው፥ ለፊተኛው አውሬ ምስል እንዲሰግዱለት ያዝዛል፡፡ ሉቃ፲፰፥፩-፯

፲፮ ወቀዳማዊሰ አርዌ ሰይጣን ውእቱ ዘቀደመ አብሶ እምኵሉ፡፡ወእቤርሰ እንተ ትቤሎ ለመኰንነ ዐመፃ ኰንነኒ እም ዕድውየ ምኩራበ አይሁድ ይእቲ እንተ ቀደመት ተፈ

፲፮ ፊተኛውም አውሬ ለመበደል ከሁሉ የቀደመ ሰይጣን ነው፥ ዓመፀኛውን ዳኛ ከባለጋራዬ ፍረድልኝ ያለችው አሮጊትም በመሠራት ከቤተክርስቲያን የቀደመች የአይሁድ

ጥሮ እም ቤተክርስቲያን፡፡ዕድውየሰ ትቤሎሙ
ለደቂቀ ቤተክርስቲያን፡እስመ አልቦሙ ስንአ
ማእከለ ደቂቀ ምኵራብ ወማእከለ ደቂቀ ቤተ
ክርስቲያን፡እስመ ክርስቶስ ገብረ ፍልጠተ
እማእከሌሆሙ ወእማከሌነ ደቂቀ ቤተ ክርስ
ቲያን በሕማማተ መስቀሉ፡፡

፲፯ ዕቤራይትሰ ተሰምየት በእንተ ዘገኈ
ሕቄት በአብዝኆ ውሉድ እመሐዛኒሃ፡፡ለአምላከ እስ
ራኤልሰ ኢወለደት ሎቱ ዘእንበለ ሕዳጣን እለ
ተነርፉ፡፡በከመ ይቤ ኢሳይያስ ሶበ አኮ እግዚአ
ብሔር ፀባኦት ዘአትረፈ ለነ ዘርአ ከመ ሰዶም
እምኮነ ወከመ ገሞራ እመሰልነ፡፡ወበእንተ ዝሙ
ታሰ አስምአ ላቲ እግዚአብሔር በነቢያቲሁ
፡፡ሕዝቅኤልኒ ይቤ ከመዝ ይቤ አዶናይ እግ
ዚአብሔር ሥረዊኪ ወዘመድኪ እምድረ ከና
ኦን አቡኪ አሞሬዎን ወእምኪ ኬጥያ፡፡ወአመ
ወለዱኪ ኢጸመሙ አጥባትኪ ወበማይ ኢሐፀ
ቡኪ ወበጼው ኢሮቱኪ ውስተ ሐፅን ኢሐፀኑ
ኪ፡፡ወኢመሐከተኪ ዐይንየ ከመ እግበር ላዕሌ
ኪ አሐተ እምእላንቶን ኵሎን ከመ እቅሥፍኪ፡፡

፲፰ ወገደፉኪ ውስተ ገጸ ገዳም ወተፅዕረት
ነፍስኪ አመ ወለዱኪ ወኀለፍኩ አንተ ኀቤኪ ወር
ኢኩኪ ትሰክቢ ውስተ ደምኪ፡፡ ወእቤ ለኪ እምደ
ምኪ ሕየዊ ወብዝኂ፡፡ወረሰይኩኪ ሠርፀ ገዳም
ወልህቂ ወዐበይኪ ወቦእኪ ውስተ አህጉር ወልሀቃ
አጥባትኪ ወበዝኀ ሥዕርትኪ ወኮንኪ ብእሲተ ወተ
ነፍሪ፡፡ወኀለፍኩ እንተ ኀቤኪ ወርኢኩኪ ከመ
በጽሐ ጊዜኪ ጊዜ እለ የኀድሩ፡፡ወሰፋሕኩ እደውየ
ላዕሌኪ ወከደንኩኪ ኃፈረተኪ፡፡ወመሐልኩ ለኪ
ወቦእኩ ኀቤኪ በሕግ ይቤ አዶናይ እግዚአብሔር
፡፡ወኮንኪ ሊተ ወሐፀብኩኪ በማይ ወሐፀብኩኪ
ደመኪ ወቀባዕኩኪ ቅብዐ ወአልበስኩኪ ዓሥቀ
ወሜላተ ወሲራየ ወአሠርኀኩኪ ሠርጐ፡፡ወወ
ደይኩ አውቃፈ ውስተ እደዊኪ ወባዝግና
ውስተ ክሳድኪ ወአፅኑገ ውስተ እእዛንኪ ወአክ
ሊለ ምክሕ ውስተ ርእስኪ፡፡ወአሰርገኩኪ ወር
ቀ ወብሩረ ወመዋጥሕኪ ሜላት ወሲራይ ወዐ
ሥቅ፡፡ወሐረስኩኪ በስንዳሌ ወመዓር ወቅብዕ
ወተሴሰይኪ ወበላዕኪ ወሰባሕኪ ወሠነይኪ
ጥቀ ፈድፋደ ወተሰምዐ ስምኪ ውስተ ኵሉ
አሕዛ ብ፡፡ሠነይኪ እስመ ፍጹም ውእቱ
ላሀይኪ ዘረ ሰይኩ ለኪ ሥነኪ ይቤ አዶናይ
እግዚአ ብሔር፡፡

፲፱ ወተወከልኪ በስንኪ ወዘመውኪ
በስምኪ ወአፈድፈድኪ ዝሙተኪ በኵሉ ፍኖ
ት ወነሣእኪ እም አልባስኪ ወገበርኪ አማልክተ

ምኩራብ ናት፡፡ የቤተክርስቲያንን ልጆች ባለጋ
ራዎች ትላቸዋለች በምኩራብ ልጆችና በቤተ
ክርስቲያን ልጆች መካከል ስምምነት የለምና፥
ክርስቶስ በእነርሱና በእኛ በቤተክርስቲያን ልጆች
መካከል በመስቀሉ መከራዎች መለየትን
አድርጓልና፡፡

፲፯ ከውሽማዎቿ ልጆችን በማብዛት ስለ
ጉበጠች አሮጊት ተባለች፡፡ ለእስራኤል አምላ ክ
ግን ከተመረጡ ከጥቂቶች በቀር አልወለ
ደችም፡፡ ኢሳያይስ አቸናፊ እግዚአብሔር ዘርን
ባያስቀርልን እንደ ሰዶም በሆንን እንደ ገሞራም
በመሰልን አለ፡፡ ስለ ዝሙቷም እግዚአብሔር በነ
ቢያቱ ተናገረባት፡፡ ሕዝቅኤልም እንዲህ አለ
አዶናይ እግዚአብሔር ሥርሽ ነው ዘመድሽም
ነው አባትሽ አሞሬዎን እናትሽም ኬጥያ
ከከናኦን ምድር ነው፥ በወለዱሽ ጊዜ እትብትሽ
አልተቆረጠም በውኃም አላጠቡሽም በጨው አል
ተቀባሽም በእቅፍ አላሳደጉሽም ከእኒያ ከሁላቸው
አንዲቱን በላይሽ እንዳደርግ እንዳልቀስፍሽም
ዓይኔ አልራራችልሽም፡፡

፲፰ በበረሀ ውስጥ ጣሉሽ
በወለዱሽም ጊዜ ነፍስሽ ተጨነቀች በአንቺ
በኩል አለፍሁ በደምሽም ላይ ተኝተሽ አየሁ
ከደምሽ ዳኚ ብዙም ሁኚ አልሁሽ የበረሀ ተክል
አደረግሁሽ አደግሽ ታላቅም ሆንሽ ወደ
ከተሞችም ገባሽ ጡትሽ አደገ ፀጉርሽም በዛ
ሴትም ሆንሽ ማፈርም ጀመርሽ፣ በአንቺ በኩል
አለፍሁ የምትታጨበት ጊዜ እንደደረሰ ዐወቅሁ
መጎናጸፊያዬን በአንቺ ላይ ዘረጋሁ አፍረትሽንም
ሸፈንሁ ማልሁልሽ ወዳንቺም በሕግ ገባሁ አለ
አዶናይ እግዚአብሔር፡፡ ለእኔ ሆንሽልኝ በውኃ
አጠብሁሽ ደምሽንም አጠብሁሽ ቅባት ቀባሁሽ
ጥሩ በፍታና ሐር ግምጃ ቀይ ግምጃም አለ
በስሁሽ በጌጥም አስጌጥሁሽ ቀለበትን በእጆችሽ
አደረግሁ የወርቅ ማርዳም በአንገትሽ ጉትቻ
በጆሮዎችሽ የመመኪያ ዘውድም በራስሽ አኖርሁ
በወርቅና በብር አስጌጥሁሽ መደረቢያሽም ሐር
ግምጃና ቀይ ግምጃ ጥሩ በፍታም ነው፥ በስን
ዴና በማር በቅባትም አረስሁሽ ተመገብሽ በል
ተሽም ሰባሽ፤እጅግም አማርሽ ስምሽም በአሕዛብ
ሁሉ መካከል ተሰማ፡፡ ያደረግሁልሽ ደም
ግባትሽ ውበትሽም ፍፁም ነውና አማርሽ አለ
አዶናይ እግዚአብሔር፡፡

፲፱ በደምግባትሽ ተማመንሽ በስምሽም
አመነዘርሽ ዝሙትሽንም በጉዳና ሁሉ አበዛሽ
ከልብሶችሽም ወስደሽ የተሰፋ አማልክትን ሠፋሽ

ርፍእ፡፡ወዘመውኪ ቦሙ ወኢቦእኪ ወኢኮንኪ ወነሣእኪ ሠርጐ ምክሕኪ ወርቅየ ወብሩርየ ዘወሀብኩኪ ወገበርኪ አምሳለ እደው ወዘመ ውኪ ቦሙ ወነሣእኪ አልባሰ ዓሥቅ ወአልበስ ኪዮሙ ቅብዕየ ወዕጣንየ አንበርኪ ቅድመ ገ ጸሙ፡፡ወእክልየ ዘሴሰይኩኪ ስንዳሌ ወቅብዐ ወመዐረ ወአብላዕኪዮሙ ወሠራዕኪ ቅድሜሆ ሙ ለመዓዛ ሠናይ፡፡ ወእምዝ ይቤ አዶናይ እግዚአብሔር ነሣእኪ አዋልድየ ዘወለድኪ ሊተ ወደቂቅየ ወሦዕኪ ሎሙ ወቀተልኪ ታስ ተናእሲኑ ዘዘመውኪ ወሦዕኪ ደቂቅየ ዝንቱ አከየ እምኲሉ ዝሙትኪ ወርኲስኪ፡፡ ወኢ ተዘከርኪ ወዋዕለ ንእስኪ ወአመ ዕራቅኪ አን ቲ ወተኀፍሪ ወጽንቅቅት አንቲ በደምኪ ሐዮ ኪ እምድኅረዝ ኲሉ አከይኪ፡ አሌ ለኪ አሌ ለኪ ይቤ አዶናይ እግዚአብሔር፡፡

፴ ወሐነጽኪ ለኪ ቤተ ኀበ ትዜምዊ ወገበርኪ ለኪ መንበረ ውስተ ኲሉ መርኅብ ወውስተ ርእሰ ፍኖት ሐነጽኪ ለኪ ኀበ ትዜም ዊ ወአርኰስኪ ሥነኪ ወቀፈጽኪ አቍያጸኪ ለኲሉ ኃላፌ ፍኖት ወአብዛኀኪ ዝሙተኪ ወዘመውኪ በደቂቀ ግብጽ መሐዛንኪ እለ ዐቢ ይ ነፍስቶሙ ወዘልፈ ትዜምዊ ምስሌሆሙ ወአቅናዕክኒ፡፡ወአነሥእ እዴየ ላዕሌኪ ወእሥ ዕር ሕገኪ ወእሜጥወኪ ለነፍሰ ጸላዕትኪ አዋል ደ ኢሎፍሊ እለ ሜጣኪ እምፍኖትኪ ወአስ ሐታኪ ወዘመውኪ ፊድፉደ እም አዋልደ ሱር ወሑድ፡፡ምስለ ከመዝ ዓዲ ኢጸገብኪ ወዘመ ውኪ ወኢያንፈስኪ ወአብዛኀኪ ኪዳነኪ በብ ሔረ ፋርስ፡፡ ወምስለ ከማሁ ዓዲ ኢጸገብኪ፡፡ ምንተ እንከ እሬስዮን ለአዋልድኪ ይቤ አዶናይ እግዚአብሔር፡፡

፴፩ ገበርኪ ዘንተ ኲሎ ግብረ ብእሲት ዘማ፡፡ወዘመውኪ ትሥልስተ ምስለ አዋልድኪ ፡፡ወሐነጽኪ ኀበ ትዜምዊ ውስተ ርእሰ ኲሉ ፍኖት ወገበርኪ መንበርተኪ ውስተ ኲሉ መር ኅብ ወከመ ከማሂ ኢኮንኪ እንተ ታስተጋብእ ደነሳ ተመሰልኪ ብእሲተ እንተ ትነሥእ ሐብ ሐባ በኀበ ምታ ወትዴንሶሙ ለመሐዛቲሃ እለ ትዜሙ ምስሌሆሙ፡፡ከማሁኬ አንቲኒ ደነስ ኪዮሙ ለኲሎሙ መሐዛንኪ ወኀለይኪዮሙ ይምጽኡ ኀቤኪ ወይመግቡኪ በዝሙትኪ ወፈ ድፈደ ዝሙትኪ እምኲሎን አንስት እለ ዘመ ዋ ምስሌኪ እስመ ደነስኪ ወኢደነሱኪ

አመነዘርሽባቸው አልገባሽም አልቆምሽም የመመ ኪያሽንም ጌጥ የሰጠሁሽን ወርቄንና ብሬን ወሰ ድሽ የወንዶችንም ምስሎች ሠራሽ፡ አመነዘር ሽባቸውም የጥሩ በፍታ ልብሶችን ወስደሽ አለበ ስሻቸው ቅባቴንና ዕጣኔን በፊታቸው አደረግሽ የመገብሁሽን ስንዴና ዘይት ማርም መገብሻቸው በፊታቸውም ለመልካም መዓዛ ሠራሽ። ከዚህም በኋላ አዶናይ እግዚአብሔር አለ የወለድሽልኝን ሴቶች ልጆቼን ወሰድሽ ልጆቼንም ሠዋሽላቸው ገደልሽም ያመነዘርሽውንና ልጆቼን የሠዋሽውን ታሳንሽዋለሽን ይህ ከዝሙትሽና ከርኩሰትሽ ሁሉ የከፋ ሆነ የልጅነትሽን ጊዜ አላሰብሽም ራቁ ትሽን ሳለሽ አፍረሽ ነበር በደምሽም የተጨ ማለቅሽ ነበርሽ ከዚህ ሁሉ ክፋትሽ በኋላ ዳንሽ ወዮልሽ ወዮልሽ አለ አዶናይ እግዚአብሔር።

፴ የምታመነዝሪበትን ቤት ለራስሽ በአደባባይ ሁሉ ዙፋን አዘጋጀሽ በዋና ጉዳናም ላይ የምታመነዝሪበትን ለራስሽ ቤት ሠራሽ ደም ግባትሽን አረከስሽ ለአላፊ መንገደኛ ሁሉ ጭና ችሽን ገለጥሽ ዝሙትሽንም አበዛሽ ሰብነታቸው በገዘፈ ውሽሞችሽ የግብጽ ልጆች አመነዘርሽ ከእነርሱም ጋር ዘወትር አመነዘርሽ አስቀናሽኝም እጄን በአንቺ ላይ አነሣሁ ሕግሽንም እሽራለሁ ከመንገድሽ ለመለሱሽ ላሳቱሽም ለጠላቶችሽ ለኢሎፍሊ ሴቶች ልጆች ነፍስ አሳልፌ እሰጥ ሽላሁ ከሱርና ከሑድ ሴቶች ልጆች ይልቅ አብ ዝተሽ አመነዘርሽ። ከዚህም ጋር እንደገና አልጠ ገብሽም አመነዘርሽም አላረፍሽምም ቃል ኪዳን ሽንም በፋርስ ሀገር አበዛሽ ከዚህም ጋር እንዲሁ ገና አልጠገብሽም እንግዲህ ሴቶች ልጆችሽን ምን አደርጋቸዋለሁ አለ አዶናይ እግዚአብሔር።

፴፩ ይህን ሁሉ የአመንዝራ ሴት ሥራ አደረግሽ፣ ሦስተኛም ከሴት ልጆችሽ ጋር አመነዘርሽ የምታመነዝሪበትንም ቤት በዋና መንገድ ሁሉ ሠራሽ መቀመጫሽንም በአደባባይ ሁሉ አዘጋጀሽ። የዝሙቷን ዋጋ እንደምትሰበስብ እንደ አመንዝራ ሴት አልሆንሽም ወዳጇን በባሏ ፈንታ የምትቀበል ሴትን መሰልሽ አብራቸው የምታመነዝር ውሽሞቿን ዋጋ ትሰጣቸዋለች እንዲሁም አንቺም ለውሽሞችሽ ሁሉ ዋጋ ሰጠሻቸው ወዳንቺም እንዲመጡ በዝሙትሽም ይመግቡሽ ዘንድ ዘፈንሽላቸው ከአንቺ ጋር ካመነዘሩት ሴቶች ሁላቸው ይልቅ ዝሙትሽ በዛ ኃጢአት ሠርተሻልና ዋጋም አልሰጡሽምና ወንጀለኛ ሆንሽ በዝሙትሽም ምክንያት

ወኮንኪ አንቲ ዕሉተ ወአፍለጥኪ በበይነ ዝሙትኪ፡፡ ስምዒ ዘማ ቃለ እግዚአብሔር ከመዝ ይቤ አዶናይ እግዚአብሔር፡፡እስመ ዘሮኪ ወርቅየ ወቀፊጽ ኪ ኃፍረተኪ በዝሙትኪ ለመሐዛንኪ በኲሉ ፍትወተ ኃጣውእኪ ወበደመ ደቂቅኪ ዘወሀብ ኪዮሙ፡፡በበይነ ዝንቱ ናሁ አስጋብኦሙ ወለ ኲሎሙ እለ አፍቀርኪዮሙ ወለኲሎሙ እለ ጸላዕኪዮሙ አስተጋብኦሙ ላዕሌኪ ወየዐግቱኪ ወእቀፍጸኪ ኀሣረኪ በቅድሜሆሙ፡፡ ኢሳ፵፯፥፩-፲፭

፳፪ ወበሆሴዕኒ አስምዐ ላቲ ወይቤ ተዋቀሥዋ ለእምክሙ እስመ ይእቲ ኢኮነት ብእሲትየ ወአነኒ ኢኮንኩ ምታ፡፡ወናሁ እሥ ዕር ዝሙታ እምቅድመ ገጽየ ወመሐዛኒሃ እማእከለ አጥባቲሃ ወእቀፍጻ ዕራቃ ወእሬስያ ከመ አመ ንእሳ፡፡ወእገብራ ከመ በድው ወእ ሬስያ ከመ ምድር ዘአልቦ ማይ ወእቀትላ በጽ ምእ፡፡ወኢይሣህሎሙ እንከ ለደቂቃ እስመ ትውልደ ዘማ እሙንቱ እስመ ዘመወት እሞ ሙ ወአስተኃፈረቶሙ ወላዲቶሙ፡እስመ ትቤ አሐውር ወእትልዎሙ ለመሐዛንየ እለ ይሁ ቡኒ ስቴየ ወመብልዕየ ወይዔርዙኒ ልብስየ ወመዋጥሕየ ወይሁቡኒ ቅብዕየ ወኲሎ ተድ ላየ፡፡

፳፫ ወበእንተ ዝንቱ ናሁ አነ አንጽር ፍኖታ በሦክ ወእፌጽም መንገደ ወተኀጥእ ምኅላፈ ወትዴግኖሙ ለመሐዛኒሃ ወተኀሥሥ ሙ ወኢትረክቦሙ፡፡ወትብል እገብእ እንከ ኀበ ምትየ ዘትካት እስመ ይኄይሰኒ ዘቀዲሙ እምይእዜ፡፡ወይእቲሰ ኢያእመረት ከመ አነ ወሀብክዋ እክለ ወወይነ ወቅብዐ ወአብዛኅኩ ላቲ ወርቀ ወይእቲሰ ወርቀ ወብሩረ ገብረት ለበዓል፡፡ወበእንተ ዝንቱ እትመየጥ ወአስተ ጋብእ እክልየ ዘበበጊዜሁ ወወይንየ ዘለለ ዕለቱ፡፡ ወእሰልባ አልባስየ ወመዋጥኅየ ከመ ኢትክድን ኃፍረታ በቅድመ መሐዛኒሃ ወአ ልቦ ዘያድኅና እምእዴየ፡ዘንተ አስምየ አስምዐ በነቢያቲሁ አኮ በእንተ ዝሙተ ሥጋ ባሕ ቲቱ አላ በእንተ ዘዘመወት በአማልክተ ግብጽ ወጢሮስ ወሲዶና ወበአማልክተ ኲሎሙ አሕ ዛብ እለ ኢተሰምየ ስመ እግዚአብሔር ላዕሌ ሆሙ፡፡ ሆሴ፪፥፩-፲፭

፳፬ እምይእዜሰ ንንግር ወንግባእ ኀበ ፍካሬ ነገር ዘይቤ ያዕቆብ ኮና ለዳን አር ዌ ምድር ዘይጸንሖ፡፡ዘንተሰ ይተረጐም ዘከመ

ተለየሽ፡ አመንዝራይቱ ሆይ የእግዚአብሔርን ቃል ስሚ አዶናይ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ወርቂን በትነሻልና አፍረትሽንም በዝሙትሽ በኃጢአቶችሽ ፍትወት ሁሉ በሰጠሻቸው የል ጆችሽ ደም ለውሽሞችሽ ገለጥሽ በዚህም ምክ ንያት እነሆ የተገናኘሻቸውን ውሽሞችሽን ሁሉ ያፈቀርሻቸውንም ሁሉ ባንቺ ላይ እሰበስባ ቸዋለሁ የጠላሻቸውንም ሁሉ በአንቺ ላይ እሰበ ስባቸዋለሁ እነርሱም ይከቡሻል ጉስቁልናሽንም በፊታቸው እገልጥብሻለሁ፡፡ ኢሳ፵፯፥፩-፲፭

፳፪ በሆሴዕም ተናገራት፣ እለም እናታችሁን ውቀሱአት እርሷ ሚስቴ አልሆ ነችም እኔም ባሏ አልሆንሁምና እነሆ ዝሙቷን ከፊቴ እሽራለሁ ውሽሞቿንም ከጡቶቿ መካ ከል እሽራለሁ ራቁትነቷን እገልጥባታለሁ በታና ሽነቷ እንደነበረች አደርጋታለሁ፡እንደ ምድረ በዳ አደርጋታለሁ ውኃ እንደ ሌለባትም ምድር አደ ርጋታለሁ በውኃ ጥምም እገድላታላሁ የአመ ንዝራ ልጆች ናቸውና ከእንግዲህ ልጆቿን ይቅር አልላቸውም እናታቸው አመንዝራለችና የወለ ደቻቸውም አሳፍራቸዋለችና ሂጀም መጠጤንና ምግቤን የሚሰጡኝን ልብሴንና መጐናፀፊያዬን የሚያለብሱኝን ዘይቴንና ተድላዬን ሁሉ የሚሰጡኝን ውሽሞቼን እከተላቸዋለሁ ብላለችና፡፡

፳፫ ስለዚህም እነሆ እኔ መንገዷን በእሾህ እጥራለሁ መንገድንም እዘጋለሁ ማለፊያ ታጣለች ውሽሞቿንም ትከተላቸዋለች ትፈልጋቸዋለች ነገር ግን አታገኛቸውም እንግ ዲህስ ከአሁኑ ይልቅ የቀደመው ይሻለኛልና ወደ ቀደመው ባሌ እመለሰላሁ ትላለች እርሷ ግን እኔ እህልና ወይን ዘይትም እንደ ሰጠኋት አላወቀችም ወርቅ አበዛሁላት እርሷ ግን ወርቅና ብሩን ለበዓል አደረገች ስለዚህም ተመልሼ እህሌን በየጊዜው ወይኔንም በየቀኑ እሰበስባለሁ በውሽሞቿ ፊት አፍረቷን እንዳትከድን ልብሶቼንና መደረቢያዬን እገፋታለሁ ከእጀም የሚያድናት የለም፡ ይህን መናገርን በነቢያቱ ተናገረባት ስለ ሥጋዊ ዝሙት ብቻ አይደለም በግብጽና በጢሮስ በሲዶናም አማልክት የእግዚአብሔር ስም ባልተጠራባቸው የአሕዛብ ሁሉ አማልክት ስላመነዘረች ነው እንጂ፡፡ ሆሴ፪፥፩-፲፭

፳፬ ከእንግዲህስ ወደ ነገሩ ትርጉም ተመልሰን እንናገር፥ ያዕቆብ ዳንን የምድር እባብ ይጠብቀዋል ያለውን እንናገር፥ ይህስ ሰይጣን

www.ethiopianorthodox.org

ይሜብል ሰይጣን በመንግሥተ ሐሳዌ መሲሕ ፡፡ ወአትሊዎ ይቤ ዘይነስኮ ሰኰናሁ ለፈረስ ወይወድቅ ዘይጼዓኖ ወእግዚአብሔር ይጼንዖ ፡፡ወምንተ ውእቱ ፈረስ ዘእንበለ ቤተክርስቲያን ቅድስት እንተ ትጸውር አስማተ ሥላሴ በከመ ኪሩቤል አፍራሲሁ ይጸውሩ ትሥልስቶ እንዘ ውእቱ ይጸውሮሙ በኃይለ መለኮቱ፡፡ በከመ ይቤ በመኃልየ መኃልይ ለፈረስየ ወለሰ ረገላተ ፈርዖን አስተማሰልኩኪ፡፡ፈርዖን ይተ ረጐም በሰይጣን ወሰረገላቲሁኒ በእለ ይጼዓን ቦሙ ለአስተማርዮ፡፡ወብሂለ አስተማሰልኩኪ በፈረስየ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር ዘይቤላ ለቤተክርስቲያን ዘቀዲሙ ነበርኪ ሰረገላሁ ለሰ ይጣን ይእዜሰ አስተማሰልኩኪ በአፍራስየ ኪሩባውያን ከመ ትኩንኒ መጸረ፡፡

፳፫ ወዘይቤሰ ይነስክ ሰኰናሁ ለፈረስ እስመ በመንግሥተ ሐሳዌ መሲሕ ይፈቅድ ሰይጣን ከመ ያእቅጻ ለቤተክርስቲያን ወበአ ስናነ ሕምዙ ይነስክ ሰኰናቲሆሙ ለመሀይም ናን፡፡ቦ ዘይትነገል ወቦ ዘይድኅን:: ወበእንተ ዘይትነገል ይቤ ወይወድቅ ዘይጼዓኖ እስመ ገደፈ ሃይማኖተ ዘላዕሌሁ፡፡ ወበእንተ ዘይድ ኅን ይቤ ወእግዚአብሔር ይጼንዖ፡፡በከመ ይቤ እግዚእነ ብዙኃን ይመጽኡ በስምየ እንዘ ይብ ሉ አነ ውእቱ ክርስቶስ ወዘአዝለፈ ትዕግሥቶ ውእቱ ይድኅን፡፡ወብሂለ እግዚአብሔር ይጼን ያሰ አኮ ፍጹመ ዘይገድፋ እግዚአብሔር ለቤ ተክርስቲያኑ ወአኮ ዘያጸርዕ አምልኮ ሥላሴ እምላዕለ መሀይምናን፡፡ቦ እለ ይድኅኑ በጕያ ውስተ አድባር ወበዐታት ወበግበበ ምድር በከ መ ይቤ ሶበሰ ኢያሕፀሮን እግዚአብሔር ለእ ማንቱ መዋዕል አልቦ ዘእምድኅን፡፡ ወባሕቱ በእንተ ኅሩያንየ የኅጽራ እማንቱ መዋዕል፡፡

፳፬ ወይእዜኒ ንንግር ዕበዶሙ ለሰብአ ኢየሩሳሌም ደቂቆሙ እለ ይጠብዉ ጥበ ሶበ ይጽርሑ ወይብሉ ሆሳዕና በኦርያም ሆሳዕና ለወልደ ዳዊት ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚ አብሔር፡፡ ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወቡሩክ አንተ ንጉሠ እስራኤል፡፡ አንክሩኬ ለዕበደ እሉ አእሩግ እለ ይቤልዎ ለእግዚእነ አዝዝ ሊቅ ከመ ያርምሙ እሉ ሕፃናት፡፡እን ዘ ሕፃን ይሌቡ፡፡መኑ ይሜህሮ ዕበደ እንዘ ይጸርሕ ከመ ቀርን፡፡ለመኑ ኢያሐውዞ ዘእንበለ ከማከሙ ዕንቡዛነ ኅሊና፡፡ለእመ ሕፃ

በሐሳዌ መሲሕ መንግሥት እንደሚሠለጥ ይተረጐማል÷ አስከትሎም የፈረሱን ሰኰና ይ ክሰዋል የተጫነበትም ይወድቃል እግዚአብሔር ግን ያበረታዋል አለ:: ኪሩቤል ፈረሶቹ በመለኮቱ ኃይል የሚሸከማቸው እርሱ ሲሆን በሦስትነቱ እንደሚሸከሙት የሥላሴን ስም የምትሸከም ቅድስት ቤተክርስቲያን ካልሆነች በቀር ፈረስ ምንድር ነው:: በመኃልየ መኃልይ በፈረሶቼና በፈርዖን ሠረገላዎች አስመሰልሁሽ እንዳለ:: ፈርዖን በሰይጣን ሠረገላዎች ምትሐት ለማሳየት በሚጫንባቸው ይተረጐማል በፈረሴ መሰልሁሽ ማለትም ቀድሞ የሰይጣን ሠረገላዎች የነበርሽ አሁን ግን ማደሪያ እንድትሆኚ በኪሩባውያን ፈረሶቼ መሰልሁሽ ብሎ ለቤተክርስቲያኑ የተናገራት የእግዚአብሔር ልጅ ቃል ነው::

፳፫ የፈረሱን ሰኰና ይነክሳል ያለውም በሐሳዌ መሲሕ መንግሥት ሰይጣን ቤተክርስቲያንን ያሰናክላት ዘንድ ይሻልና በጥ ርሶቹም መርዝ የምእመናንን ተረከዞቻቸውን ይነክሳል የሚጠፉ እና የሚድንም አለ:: ስለ ሚጠፋው የሚጫንበት ይወድቃል አለ÷ በእርሱ ያለውን ሃይማኖት ትቷልና÷ ስለ ሚድነውም እግዚአብሔር ያበረታዋል አለ:: ጌታችን በወ ንጌል ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉ ትዕግሥትን ያዘወተረ እርሱ ይድናል እንዳለ:: እግዚአብሔር ይጠብቀዋል: ማለት ግን እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኑን ፈጽሞ የሚተ ዋት አይደለም ሥላሴን ማምለክንም ከምእመናን የሚያጠፋ ሆኖ አይደለም:: እግዚአብሔር እኒያ ን ቀናት ባያሳጥራቸው የሚድን ባልኖረ:ነገር ግን ስለ ምርጦቼ እኒያ ቀናት ያጥራሉ እንዳለ ወደ ተራሮችና ወደ ዋሻዎች ወደ ፍርኩ ታዎችም በመሸሽ የሚድኑ አሉ:: ማቴ፳፬፥፳፪

፳፬ አሁንም የኢየሩሳሌምን ሰዎች ስንፍናቸውን እንናገር ጡት የሚጠቡ ሕፃናቶቻቸው ሆሣዕና በአርያም ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተመሰገነ ነው ለእግዚአብሔር በሰማያት ምስጋና ይሁን አንተም የእስራኤል ንጉሥ ሆይ የተመሰገንህ ነህ እያሉ በጮሁ ጊዜ መምህር ሆይ እኒህ ሕፃናት ዝም እንዲሉ እዘዝ ያሉትን የእኒያን ሽማግ ሌዎች ስንፍና አድንቁ::ሕፃን እግዚአብሔርን ሲያመሰግነው ምን ዝም ያሰኛል::ሕፃን ሲያስ ተውል እንደ ነጋሪት እየጮኸ ማን ስንፍናን ያስተምረዋል:: አዕምሮአችሁን የሳታችሁ ሆይ እንደ እናንተ ላለው ካልሆነ በቀር ማንንም

ናት አርመሙ በአይቴ ይትፌጸም ዘተብህለ ስምዑ ለእግዚብሔር እሙን ወያጠብብ ሕፃና ተ፡፡ለእመ ሕፃናት አርመሙ በአይቴ ይትፌ ጸም ዘተብህለ እስመ ጥበብ ከሠተት እዝነ ጽምምተ ወልሳነ ሕፃናት ረሰየት ርትዕተ፡፡
ማቴ፳፭፥፲-፲፭

፳፯ ወይእዜኒ ንግበር በዓለ በቃለ ይባቤ እንዘ ንብል ስብሐት በአርያም ለዘተ ወልደ እምአብ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም፡፡ ሆሳዕና ለወልደ ዳዊት ለዘተሠገወ እምቅድ ስት ድንግል፡፡ዝ ውእቱ አሐዱ ክርስቶስ በመ ለኮቱ ወበትስብእቱ ኅቡር በኢቱሳሔ ወድ ሙር በኢሙያጤ፡፡ህየንተ አዕፁቀ ዘይት ንን ሣእ ለነ መስቀለ፡፡ወህየንተ ፀበርተ ተመርት ንጸር ወንጌላተ፡፡ወህየንተ ቤተመቅደስ አይሁ ዳዊት ንዑዳ ለቤተክርስቲያን፡፡ ህየንተ ታቦት እንተ ውስቴታ ኦሪት ነአምኃ ለማርያም እን ተ ትጸውር ለነ እስካለ በረከት፡፡ንሕዩ በክር ስቶስ ወነህሉ በክርስቶስ ወንድኅን በክርስቶስ እስከ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

........ /// ........

አያስደስተውም፥ ሕፃናት ዝም ቢሉ የእግዚ አብሔር ምስክርነት የታመነ ነው ሕፃናትንም ዐዋቆች ያደርጋል የተባለው በየት ይፈጸማል? ሕፃናት ዝም ካሉ ጥበብ የደነቆረችይቱን ጆሮ ከፈተች የሕፃናትንም አንደበት የተከነዋወነች አደረገች የተባለው በሄት ይፈጸማል፡፡
ማቴ፳፭፥፲-፲፭

፳፯ አሁንም ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ ከአብ ለተወለደ ለርሱ በአርያም ምስጋና ይሁን፥ ሆሣዕና ከቅድስት ድንግል ለተወ ለደው ለዳዊት ልጅ እያልን በእልልታ ቃል በዓል እናድርግ፡፡ በመለኮቱና በሰውነቱ ያለመቀ ላቀል አንድ የሆነ ያለመለወጥም የተዋሀደ አንዱ ክርስቶስ ይህ ነው፡፡ ስለ ወይራ ዝንጣፊ ፈንታ መስቀልን ለራሳችን እንያዝ፥ስለ ሰኔል ዝንጣፊም ፈንታ ወንጌልን እንያዝ፥ ስለ አይሁዳዊት ቤተ መቅደስም ፈንታ ቤተ ክርስቲያንን እንዞራት ፥ኦሪት በውስጧ ስላለባት ታቦት ፈንታ የበረከት ፍሬ የተሸከመችልን ማርያምን እጅ እንንሣት ፥በክርስቶስ ሕያዋን እንድንሆን በክርስቶስ እን ኖር ዘንድ በክርስቶስም እንድን ዘንድ እስከ ዘላለም ድረስ አሜን፡፡

........ /// ........